ግብርና ሚኒስቴር

# ለግብርና ግብአት አቅርቦትና አገልግሎት ማዕከላት የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ

---

**ቁጥር 455/2013**

**አዲስ አበባ**
**የካቲት 2011**

መግቢያ

የተሻሻለ የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት ሥርዓት በሀገሪቱ ማስፋፋት ለአ/አደሮች፣ለአርብቶ አደሮች እና ለአልሚ ባለሃብቶች የግብርና ግብዓትን ተደራሽነት በማረጋገጥ ለግብርና ምርትና ምርታማነትን ዕድገት፤የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው:: በሀገራችን ለበርካታ ዓመታት ሲተገበር የቆየው የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ግብይት ሥርዓት ከፍተኛ የሆነ የመንግስት በጀት ሲጠይቅ የቆየና የተራዘመ የግብይት ሰንሰለት የነበረው ነው፡፡ ይህም የግብዓት አቅርቦቱ በሚጠበቀው ጥራት፣ መጠን፣ ጊዜ፣ ቦታ፣ ተወዳዳሪ ዋጋ፤ በተጠያቂነት እና ቀልጣፋ በሆነ አገልግሎት እንዳይከናወን አድርጎታል፡፡ አልሚ ባለሃብቱንም በበቂ ደረጃ ባሳተፈ መልኩ ያልተከናወነና የተጠቃሚውን ተደራሽነት ያላረካ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ተጠቃሚው ከግብዓት በተጨማሪ ስለአጠቃቀሙ እና ስለ ጉዳቱ፣የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ግብዓቶች ጥቅም ላይ የዋሉ መያዣዎቻቸው አወጋገድ በባለሙያ የተደገፈ በቂ መረጃ ስለማያገኝ ለገንዘብ፣ ለጤና፤ ለአካባቢ ጥበቃና ተያያዥ ችግሮች አጋልጦታል፡፡

ይህን ችግር ከግምት በማስገባትም የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ግብይት ሂደት የተደራጀና የዘመነ ለማድረግ በቀጥታ ግብዓት ግብይት እና በአንድ ማዕከል ግብዓትን የማቅረብ ሥራ በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ የተገኘውን መልካም ተሞክሮ ከግምት በማስገባት በአንድ ማዕከል ደረጃ ግብዓት ማቅረብ እና የምክር አገልግሎትን መስጠት አሰራርን በማስፋት እና በማዘመን፣የግብዓት ተደራሽነትን ማረጋገጥ አስፈላጊነቱ ታምኖበታል፡፡ ስለዚህም አመቺ የህግ ምህዳር በመዘርጋት ማዕከላት የሚያቋቁሙ ባለሃብቶችን ማበረታታት፣የግብዓት ተጠቃሚውን ፍላጎትና መብት ማስጠበቅ እና የግብዓት ተደራሽነት ማረጋገጥ እንዲያስችል ይህ የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት ማዕከላት ለማቋቋምና ለማስተዳደር የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አውጭው ባለስልጣን

የግብርና ሚኒስቴር ስለዕጽዋት ዘር በወጣ አዋጅ ቁጥር 782/2005፣ በጸረ-ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 674/2002፣ በማዳበሪያ ማምረትና ንግድ አዋጅ ቁጥር 137/91፣ በእንስሳት መድሃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004 እና በዕጽዋት ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 56/1963 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ ለግብርና ግብአት አቅርቦትና አገልግሎት ማዕከላት የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 455/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. ትርጉም

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

3.1. “ማዕከል” ማለት የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ነው፡፡

3.2. “የግብርና ግብዓት” ማለት ዕውቅና የተሰጣቸው የሁሉም ዓይነት የሰብልና መኖ ዘሮች፤የእርሻ መሳሪዎች፣ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ማዳበሪያና ኖራ፣ የእንስሳት መድሀኒቶችና መገልገያ ቁሳቁስ፣ የእንስሳት እርባታ ግብዓቶች፣ የማነቢያ ቁሳቁስ፣ ወተት ማቀነባበሪያ መሳሪያዎች፣ የአንስሳት መኖና ጥሬ ዕቃ፣ ለዕጽዋት ጥበቃ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች፣የሰዉነት መከላከያ ትጥቅ፣ የቅድመ እና ድህረ ምርት የእርሻ መሳሪያዎች አገልግሎት፤ የመስኖ ግብርና ቴክኖሎጂዎችን ያካትታል፡፡

3.3. “አገልግሎት” ማለት እንሰሳት ማዳቀል፣ የእንስሳት ህክምና ክሊኒክ፣ ለሰብል ጥበቃ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች ርጭት፣ የተባይና በሽታ ልየታ፣ የቅድመ እና ድህረ ምርት የእርሻ መሳሪያዎች የአጠቃቀም ስልጠናና፣ የሠርቶ ማሳያ ስራና የምክር አገልግሎት ያካትታል፡፡

3.4. “ግብይት” ማለት የግብርና ግብዓቶችና አገልግሎትን ለተጠቃሚው በመሸጥ ገቢ ማግኘት ነው፡፡

3.5. “የግብርና ግብዓት አከፋፋይ ማዕከል” ማለት አግባብ ካለው አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘ፣ በዚህ መመሪያ መሠረት መስፈርቱን ያሟሉ፣ ምንጫቸው የታወቁና የተመዘገቡ ግብዓቶችን በማምረት ወይም ከውጭ በማስገባት ወይም የማከፋፈል ውክልና ወስዶ በዚህ መመሪያ መስረት ለሚቋቋሙ ማዕከላት የሚሸጥ ሰው ነው፡፡

3.6. “አግባብ ያለው አካል” ማለት የግብርና ግብዓትንና አገልግሎት ጥራት ለመቆጣጣር በፌደራልና በክልል ህጎች ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

3.7. “የግብዓት ቸርቻሪ ማዕከል” ማለት አግባብ ካለው አካል ግብዓትን ለተጠቃሚው እንዲቸረችር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማዕከል ነው፡፡

3.8. “የግብዓት አስመጪ” ማለት ግብዓትን ከአገር ውጭ ለማስገባትና ለአከፋፋዮች ለመሸጥ ከግብርና ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ የግልም ሆነ የመንግስት ድርጅት ወይም የኅብረት ሥራ ማህበር ነው፡፡

3.9. “ተጠቃሚ” ማለት ግብዓትና አገልግሎትን ከማዕከል በመግዛት/በማግኘት በአነስተኛ ይዞታ ሆነ በሰፋፊ መሬት በመጠቀም የግብርና ልማት ሥራ ለመስራት የተሰማራ ሰው ነው፡፡

3.10. “ህጋዊ ሰነድ” ማለት ይህን መመሪያ ለማስፈፀም አግባብ ካለው አካል የሚሰጥ



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

ማረጋገጫ መስፈርት ላይ የተጠቀሰና ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ሰነድ ነው፡፡

3.11. *"ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤*

3.12. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

4. የተፈጻሚነት ወሰን

በዚህ መመሪያ አንቀጽ አንድ በተጠቀሱት አዋጆች የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው

4.1. በግብርና ግብአት አቅርቦትና አገልግሎት ማዕከላት ላይ ሆኖ

4.2. ግብዓትን ለማከፋፈል ወይም ለመቸርቸር እንዲሁም አገልግሎት ለመስጠት የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት በሚጠይቅና ባገኘ አካል ላይ ነው፡፡

5. የመመሪያው ዓላማ

የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት ማዕከላትን በማቋቋምና በማስፋፋት በአንድ ማዕከል ሁሉንም ግብርና ግብዓቶች አቅርቦት ለተጠቃሚው በዓይነት፣ በመጠን፣በጥራት፣ በጊዜና በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ የሚያደርግ እና አገልግሎት የሚሰጥ ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ማዕከል ለማቋቋም መሟላት ያለባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች

6. ማንኛውም ሰው፡-

6.1. የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ብቃት ያለው ማዕከል ለማቋቋም እንደ ግብዓቱ ዓይነት አግባብ ላለው አካል በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ መሰረት ጥያቄውን ማቅረብ ይኖርበታል፤

6.2. ማእከል ለመገንባት መዋዕለ ንዋይ ከማፍሰሱ በፊት ማዕከሉ የሚቋቋምበት ቦታ ከሰው እና ከእንስሳት መኖርያ ሊኖረው የሚገባውን የአካባቢ ተጽዕኖን አስመልክቶ የጤና እና የአካባቢ ጥበቃ የሚመለከተው አካል ያወጣቸውን መስፈርቶች ስለማሟላቱ አስቀድሞ ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

6.3. ማዕከል ለማቋቋም መሰረተ ልማት ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚያበቃውን የማዕከል ህንጻ ዲዛይን አግባብ ካለው አካል መውሰድ ይጠበቅበታል፤

6.4. በማዕከልነት የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ ሰው መሰማራት የሚችለው የብቃት ማረጋገጫ ባገኘበት የአከፋፋይነት ወይም የቸርቻሪነት እና አገልግሎት ሰጪነት ብቻ ነው፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

6.5. ማንኛውም በቸርቻሪነት የተመዘገበ ማዕከል በግብዓት አከፋፋይነት ለመሰማራት ከፈለገ ለአከፋፋይነት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች በማሟላት ተጨማሪ የብቃት ማረጋገጫ አግባብ ካለው አካል ሊያገኝ ይገባል።

## ክፍል ሦስት

## የማእከል የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

7. እንደሚሰማራበት የግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት ለየግብዓቱ ጥራት ቁጥጥር አግባብ ያለው አካል ያወጣቸው መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውም ሰው የማዕከል የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት፦

7.1. በማእከል የሚሰጡ አገልግሎቶችን አሟልቶ እንደሚሰጥ የሚያረጋግጡ ህጋዊ ሰነዶችን አግባብ ያለው አካል ካዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፤

7.2. የሚያቀርባቸው ህጋዊ ሰነዶች እንደሚሰማራበት ስነምህዳር (አከባቢ) ከአርሶ/አርብቶ አደር እና አልሚ ባላሃብት ፍላጎት አንጻር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እና አገልግሎት ዓይነት ያካተተ ሆኖ ለየግብዓቶቹ አግባብ ያለው አካል ባወጣው መስፈርት መሰረት የሚወሰን ይሆናል፤

7.3. በማዕከልነት የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት

፩/ በዕዝል አንድ ላይ ተያይዞ የቀረበውን የማዕከል ዲዛይን ማሟላት ይኖርበታል፤

፪/ አንድ የተሟላ ማዕከል የሚከተሉትን ክፍሎች ማካተት ይኖርበታል፤

ሀ/ የእንስሳት መድሃኒት መጋዘን እና መሸጫ

ለ/ ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ ግብዓቶች መጋዘንና መሸጫ

ሐ/ የዕፅዋት ዘር( የመኖ ዘር፤የጓሮ አትክልት ዘር፣ የመስክ ሰብሎች ዘር፣ የፍራፍሬ ዘር ወዘተ..) መጋዘንና መሸጫ ቦታ

መ/ የተመጣጠነ መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ መጋዘንና መሸጫ

ሠ/ የአፈር ማዳበሪያ የአግሮ-ኬሚካል መጋዘን እና መሸጫ

ረ/ የቤተ-ሙከራ ክፍሎች

ሰ/ የስልጠና ክፍል

ሸ/ የቢሮ ክፍሎች

ቀ/ የመጸዳጃ እና መታጠቢያ ክፍሎች

በ/ የመጀመሪያ ዕርዳታ መስጫ ኪት

ተ/ የእርሻ መሣሪያዎች መጋዘንና መጠለያ እና

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic ... Ministry of Agriculture

ቸ/ አገልግሎት ላይ የዋሉ የፀረተባይ እና የእንስሳት መድሃኒት መያዢያ ዕቃዎች ጊዜያዊ ማከማቻ መጋዘን እና በተጨማሪ በጊቢዉ ዉስጥ የደረቅ ቆሻሻና የመሳሰሉ ቁሳቁሶች ማቃጠያ (incinerator) ይኖረዋል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9.3./፫ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ ማሟላት የሚጠበቅበት የማዕከል የክፍሎች እና መጋዘን መስፈርት ሊያቀርበው በፈለገው ግብዓት እንዲሁም አገልግሎት ዓይነትና መጠን አግባብ ባለው አካል የሚወሰን ይሆናል፤

፬/ በማዕከሉ የሚቸረቸረው የግብዓት መጠን ለየግብዓት ዓይነቱ የሚመለከተዉና አግባብ ያለው አካል የወሰነው መጠን ይሆናል፡፡ ነገር ግን ያልተወሰነላቸው ከሆነ በአከባቢው ፍላጎት መሰረት ይወሰናል፤

፭/ የዚህ አንቀጽ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ የእንስሳት ክሊኒክ እና የማዳቀል አገልግሎትን በማዕከሉ ለማካተት

ሀ/ የክልል አግባብ ያለው አካል ባወጣው መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

ለ/ በዚህ መመሪያ ዕዝል አንድ የተጠቀሰው የማዕከል ዲዛይን የእንስሳት ክሊኒክና ማዳቀል አገልግሎትን ስለማያካትት ለክሊንክ እና ማዳቀል አገልግሎት የሚውል ግንባታ ዲዛይን የክልሉ አግባብ ያለው አካል ባወጣው መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

7.4. የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ወይም ብክለት ቅነሳ መስፈርቶች

አግባብ ያለው አካል ስለ አካባቢ ጥበቃ በመመሪያው የገለጸው ዝርዝር መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕከል የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚፈልግ አካል፡-

፩/ የሚሠራው ማዕከል የአካባቢ ጥበቃ መመሪያን መሰረት ባደረገ መልኩና ብክለት ቀናሽ የሆኑ ስትራቴጅዎችን በመጠቀም መገንባቱን፤

፪/ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውና የተበላሹ ግብዓቶችና መያዣ ቁሳቁስ ከአካባቢ ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ መጠቀምና ማስወገድ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን፤

፫/ ቋሚ እና ጊዜያዊ ሰራተኞችም ከኬሚካል ጋር ግንኙነት ያለው ስራ ሲሰሩ የጤና ደህንነታቸው ማረጋገጥ የሚያስችሉ ቁሳቁሶችን መሟላታቸውን እና ከስራው ጋር የተያያዘ የጤና ምርመራ የሚደረግበት ሥርዓት መኖሩን፤አረጋግጦ መቅረብ ይኖርበታል፤

7.5. ማዕከሉ የብቃት ማረጋገጫ ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ታህሳስ 30 ባለዉ ጊዜ ማሳደስ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ ማዕከል መብትና ግዴታዎች

8. የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ ማዕከል መብቶች

   8.1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከማግኘቱ በፊት መሟላት ስለሚያስፈልጉ መስፈርቶች አግባብ ካለው አካል ያለ ምንም ክፍያ በጽሁፍም ሆነ በቃል ምክር የማግኘት መብት አለው፤

   8.2. በዚህ መመርያ መስፈርቶችን መሰረት በተገነባው ማዕከል ግብዓቶችን የማቅረብና የማሰራጨት መብት አለው፤

   8.3. ግብዓቶችን ከግብዓት ከአከፋፋይ ገዝቶ በራሱ ማዕከል መቸርቸር ይችላል፤

   8.4. የማእከሉ ባለሙያዎች በመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ባለሆኑ ድርጅቶች በሚዘጋጁ ተያያዥ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች መሳተፍ ይችላሉ።

9. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘ ማዕከል ግዴታዎች

   9.1. ማዕከሉ እያንዳንዱ ግብዓትና አገልግሎት በሚጠይቀዉ መስፈርት መሠረት አስፈላጊዉን ሙያ እና ክህሎት ያለው የሰዉ ኃይል ማደራጀት ይኖርበታል፤

   9.2. በተለያዩ ግብዓቶች ለምክርና አገልግሎት ለመስጠት የተቀጠሩ ባለሙያዎች ማእከሉ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካገኘ በኃላ በማዕከሉ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤ አግባብ ባለው አካል እውቅና ያላገኙ ባለሙያዎች በማዕከሉ ማሳማራት የለበትም፤

   9.3. የሚያቀርባቸው የግብርና ግብዓቶች በአካባቢው ተጠቃሚዎች ተፈላጊ የሆኑና ከሕጋዊ አምራች ወይም ከውጭ አስመጪ ከሆኑ ተቋማት የተገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥና ይኖርበታል፤

   9.4. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካገኘበት የግብርና ግብዓት ውጭ ሌላ መሸጥ አይችልም፤

   9.5. አግባብ ያለዉ አካል ማዕከሉን ለመፈተሽ በሚፈልግበት ጊዜ ያመተባበርና መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

   9.6. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን በማዕከሉ በሚታይ ቦታ የማስቀመጥ ግዴታ አለበት፤

   9.7. ለግብዓት ተጠቃሚዎች ለሚሸጡላቸው ግብዓት በአጠቃቀም ተገቢውን ምክር መስጠት አለባቸው፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

9.8. የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውና አገልግሎት የማይሰጡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የሚመለከተዉ ባለሙያ ተመልክቶ በሚሰጠዉ አቅጣጫ እና በሚወጣው መመሪያ መሰረት በአግባቡ አስቀምጦ ለማስወገድ መተባበር አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት አግባብ ያላቸው አካላት ቅንጅታዊ ኃላፊነት

ማዕከላቱ ከአንድ በላይ ግብዓትና አገልግሎት ስለሚሰጡ የእነዚህን ግብዓቶችና አገልግሎቶች ተቆጣጣሪ አካላት በመቀናጀት ቁጥጥር እንዲያደርጉ የሚመቻች ሆኖ፡

10. በአንድ አግባብ ባለው አካል/ተቋም/ ሥር የሚሰጡ የተለያዩ ግብዓት ግብይትና አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ሂደቶች በሚከተለው አመራጮች ማስተናገድ ይቻላል፤

10.1. የአንድ ማዕከል የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ አገልግሎት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም አግባብ ባለው የክልል ቢሮ ሥር በሚደራጅ ክፍል ሊሰጥ ይችላል፤ ወይም

10.2. ለእያንዳንዱ ግብአት የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠ በኃላ አግባብ ላለው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሠጪ አካል ሲገለጽ ግን በአንድ ተቋም ሥር ለሚተዳደሩ ግብዓቶች አንድ የተጠቃለለ የምስክር ወረቀት ከመሸኛ ጋር አባሪ አድርጎ ሊልክ ይችላል፤ወይም

10.3. ማዕከሉ የሁሉንም ግብዓቶችና አገልግሎቶች መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ በአንድ የምስክር ወረቀት የብቃት ማረጋገጫ ሊሰጥ ይችላል፤ ወይም

10.4. ለእያንዳንዱ የስራ ዘርፍ የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ለንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሰጪ አካል በመሸኛ ደብዳቤ አባሪነት ሊልክ ይችላል፤

10.5. ግብርና ሚኒስቴር ወይም ግብርናን የሚመለከተው አግባብ ያለው የክልል አካል ከቀረቡት የአፈጻጸም አማራጮች የተሻለ ቅልጥፍና ያለውን አይቶ ሊወስን ይችላል፡፡

11. የማዕከል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚወስደውን ጊዜ በተመለከተ

11.1. አመልካቹ ማመልከቻውንና ሌሎች ደጋፊ ሰነዶችን በበይነ መረብ ሥርኣት፣ በፖስታ ወይም በአካል ማቅረብ ይችላል፤

11.2. አግባብ ያለው አካል አስፈላጊ ሰነዶቹ እንደደረሱት

ሀ/ በበይነ መረብ ሥርዓት ከሆነ በአንድ ቀን ጊዜ ውስጥ፤

ለ/ በፖስታ ቤት ከሆነ ለፖስታ አገልግሎት ተቋም መቀበሉን ወዲያኑ ያረጋግጣል፤ ወይም

ሐ/ በአካል ለአምልካቹ ወይም በህጋዊ ወኪል ሰነዶችን ባቀረበበት እለት መቀበሉን ያረጋግጣል፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር The Federal Democratic Republic ...pia Ministry of Agriculture

11.3. አግባብ ያለው አካል የቀረቡለትን ሰነዶች በመመርመር መስፈርቶች መሟላታቸውን ወይም አለመሟላታቸውን ለአመልካቹ ሰው በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ መግለጽ ይኖርበታል፤

11.4. አስፈላጊው ሰነዶች መሟላታቸውን ካረጋገጠበት ጊዜ አንስቶ በአስር የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ በአካል ሄዶ የመሰረተ ልማትና ሌሎች መስፈርቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ ሪፖርት ያቀርባል፤

11.5. አግባብ ያለው አካል የሰነድና የመስክ መስፈርቶች መሟላታቸውን ባረጋገጠበት እስከ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ ይሰጣል ወይም ያልተሟሉ መስፈርቶች ካሉ እንዲሟሉ ለአመልካቹ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚታደስበት የሚታገድበትና የሚሰረዝበት ሁኔታዎች

12. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚታደስበት፣ የሚታገድበትና የሚሰረዝበት ሁኔታ የተጠቀሰውን ግብዓት ጥራት እንዲቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው አግባብ ያለው አካል ባወጣቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

13. በአንቀጽ 14 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማዕከሉ ከሚያቀርበዉ ግብዓትና አገልግሎት በአንደኛዉ አግባብ ያለዉ አካል ያወጣቸዉን ህጎች፤ ደንቦችና መመሪያዎችን በተደጋጋሚ ተላልፎ ከተገኘ እና እንዲያስተካከል ወይም እንዲያሟላ የቃልና የፅሑፍ እርማት ተሰጥቶት ማሟላት ካልቻለ ይህን ግብዓትና አገልግሎት እንዳይሸጥ ይታገዳል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. ቅሬታና ቅጣት

ቅሬታና ቅጣትን በተመለከተም ግብርና ሚኒስቴር እና ግብዓት ጥራት እንዲቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው አግባብ ያለው የክልል አካል ባወጧቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

15. የመተባበር ግዴታ

ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ሁሉም የሚመለከተው ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

16. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ግብርና ግብአት አቅርቦትና አገልግሎት ማዕከላትን አስመልክቶ ከወጣው ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም መመሪያና የአሰራር ሥርዓት ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

17. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ


ይህ መመሪያ **ከመጋቢት 2ቀን 2011 ዓ.ም** ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ዑመር ሁሴን

ግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

ዕዝል1፡ የግብርና ግብዓቶች መሸጫና መከዘኛ የውስጥ የህንጻ ዲዛይን




የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture